# 2019-20 መመሪያዎች

# የ"waste free" ማህበረሰብ ወጪ መጋራት

## ማመልከቻዎች ማስገባት የሚቻለው እስከ 5:00 PM መጋቢት 22, 2019 ነው

የሲያትል የማህበረሰብ አገልግሎቶች (SPU) የወጪ መጋራት እገዛ/ድጋፍ ማመልከቻዎችን በመቀበል ላይ ነው። ይህም ብክነት በመከከላከል ላይ ለሚያተኩሩት ነው፡፡ ብክነት መከላከል ማለት አነስተኛ መጠንን በመግዛት እና በመጠቀም፣ እንደገና መጠቀም የሚቻሉትን በመጠቀም ወይም እቃዎችን ሌሎች እንደገና ይጠቀሙባቸው ዘንድ ለሌሎች በመደገም ብክንነትን መቀነስ ማለት ነው፡፡ ብክነትን በምንከላከልበት ወቅት፣ አካባቢውን፣ የማህበረሰብን ጤና እየረዳን፣ ማህበረሰቡን እየገነባን እና ገንዘብ በማዳን ላይ ነን፡፡

የግራንት ፕሮግራም አላማ

- የማህበረሰብ አመራር እና ፈጠራን በብክነት መከላከል ዙሪያ መደገፍ
- ማህበረሰቡ ብክነትን የሚከላከልበት እድል እንዲጨምር ማድረግ
- ሲያትል ውስጥ ወደ ብክነት የሚሄዱ ማቴሪያሎችን መቀነስ

ፈንድ ማድረግ

- ለ 2019-20 ግራንት ኡደት አጠቃላይ $100,000 የሚሆን ገንዘብ አለ፡፡
- የግራንት ጥያቄ ከ $5,000 እስከ $20,000 ያክል ሊሆን ይችላል፡፡ SPU ከዚህ የሚያንስ ወይም የሚበልጥ መጠንን ግራንት ለማድረግ መብት አለው፡፡
- ግራንት ገንዘብ ተከፋይ የሚደረገው በተከታታይ ክፍያ መሰረት ነው፡፡
- የግራንት ፈንድ ፕሮጀክቱ በተጀመረ በ 12 ወራት ውስጥ ሊያለቅ ያስፈልጋል፡፡ ግራንቱ ተከታታይ የሆነ/በቀጣይነት ፈንድ አይሰጥም፡፡

## ማመልከት ያለበት ማን ነው

SPU ከስር የተጠቀሱትን ኣመልካቾች ያበረታታል:

- ለትርፍ ያልተቃቃሙ/ያልሆኑ
- የማህበረሰብ እና ጎረቤት ቡድኖች
- ድርጅቶች
- ትምህርትቤቶች፣ ኮሌጆች እና ዩንቨረሲቲዎች
- ተቋማት (ማለትም እንደ ጤና እንክብካቤ ወይም ቤት አገልግሎት)
- እምነትን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች
- የወጣቶች እና ልጆች ፕሮግራም

አመልካቾች ከአንድ በላይ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ፣ ነገር ግን መቀበል የሚችሉት አንድ ሽልማት ብቻ ነው

አመልካቾች የገንዘብ እርዳታ ለመቀበል የዋሽንግተን እስቴት እና የሲያትል ከተማ የንግድ ፍቃድ ሊኖራቸው ያስፈልጋል ፣ ወይም ለሚያስፈልገው ፈቃድ በገንዘብ ያዥ በኩል መስራት ይችላል፡፡ ለፕሮጀክትዎ የተፈቀደውን እርዳታ ለመቀበል እና ለማስተዳደር ገንዘብ ያዥ ሃላፊነት አለበት፡፡ ገንዘብ ያዡ ከተፈቀደው እርዳታ ላይ 10% ሊቆርጥ ይችላል፣ ከተፈቀደው እርዳታ ላይ የሚቆረጥ ይሆናል፡፡

**የሲያትል ከተማ ንግድ ፈቃድ መረጃ:** https://www.seattle.gov/licenses/get-a-business-license/cost-of-a-business-license፡፡
**የዋሺንግተን ከተማ ንግድ ፈቃድ መረጃ:** http://bls.dor.wa.gov/faqlicense.aspx

## በድጋሜ ማመልከት

አመልካቾች ለእያንዳንዱ የፍቃድ ድጋፍ ዑደት ድጋሜ በዚህ መንገድ ማመልከት ይችላሉ:

- ድጋፍ ላልተሰጠው ፕሮጀክት ማመልከቻ ድጋሜ በማስገባት፡፡ ለሚቀጥለው የድጋፍ ዑደት ለሚያስገቡት ማመልከቻ እንዴት ማሻሻል እንደሚገባዎት ለማወቅ እኛን እንድታነጋግሩን እንመክራለን፡፡
- ለአዲስ ፕሮጀክት ማመልከቻ ማስገባት፡፡
- አንድን ፕሮጀክት ለማስፋት ወይም የሚቀጥለውን ክፍል ተግባራዊ ለማድረግ ማመልከቻ ማስገባት፡፡ ማመልከቻው ከፍተኛ የቆሻሻ መከላከያን ማሳየት አለበት፡፡ የተፈቀዱ ድጋፎች በዚህ ጊዜ የሚገኝን የቆሻሻ መከላከያ ደረጃዎችን ለማስቀጠል ላይውሉ ይችላሉ፡፡

## የፕሮጀክት መስፈርት

ለማመልከት ፕሮጀክቶቹ የሚከተለውን ሶስት መስፈርቶችን ሊያሟሉ ያስፈልጋል፡

1. ፕሮጀክቶቹ በሲያትል ከተማ ክልል ውስጥ የመፈፀሙ መሆን አለባቸው ወይም በሲያትል ውስጥ ቀጥተኛ ተፅእኖ ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

   አመልካቾች ከሲያትል ውጪ ሊገኙ ይችላሉ፣ ፕሮጀክቱ ሲያትል ላይ የሚያተኩር ከሆነ፡፡

   የሲያትል ከተማን ድንበር ካርታ በድረገጽ ማየት ይችላሉ፡ **http://clerk.ci.seattle.wa.us/~public/nmaps/fullcity.htm**

2. ፕሮጀክቶች ብክነትን በመከላከል ላይ ሊያተኩሩ ያስፈልጋል፡፡ ምሳሌዎች የሚከተለውን ያካትታሉ፡

   - ማህበረሰቡ እንዴት አድርጎ ብክነትን መከላከል እንደሚችል ማስተማር
   - አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮችን መቀነስ ማለትም የሚቆዩ የምግብ እና የመጠጥ ማስቀመጫዎች ማስታወቂያ
   - የተበላሹ መሳሪያዎችን ሰዎች እንዴት አድርገው ማስተካከል እንደሚችሉ ለማስተማር ወርክሾፕ ማዘጋጀት
   - ሬስቶራንት ውስጥ የምግብ ብክነትን ለመቀነስ አዳዲስ ስልቶችን መሞከር
   - ምግብ እና ሌሎች ነገሮችንም ለመጋራት የሚያስችል መተግበሪያ መፍጠር
   - እያንዳንዱ ሰው አንድ አንድ ከሚገዛ ይልቅ እንደማህበረሰብ አንድን መሳሪያ በመግዛት መዋዋስ
   - ምግብ፣ ልብስ እና ሌሎች እቃዎችን ሌሎች መጠቀም ይችሉ ዘንድ እርዳታ ማድረግ
   - የትምህርትቤትን የምግብ እና የውስጥ ቆሻሻ ማከማቻን ወደ ኮምፖስት መስሪያነት መቀየር ወይም የማህበረሰብ አረንጓዴ ቦታ ማድረግ
     የትምህርት ቤት ወይም የማህበረሰብ መናፈሻ ቦታ ማድረግ
   - ብክነትን ለመከላል እርሶ ያለዎት ሌሎች የፈጠራ ሀሳቦች!

   ግራንቱ በሚከተሉት ላይ ሚያተኩሩ ፕሮጀክቶችን ፈንድ <u>አያደርገም</u>:

   - መልሶ መጠቀም
   - በሌላ ቦታ ላይ የሚደረግ ኮምፖስቲንግ (ፕሮሰስ ተደርጎ ሌላ ቦታ የሚሸጥ)
   - የብስክሌት ማጋራቶች እና የመኪና ማጋራቶች




3. ፕሮጀክቶች ከሚከተሉት ውስጥ <u>አንድ ወይም ከዚያ በላይ</u> የሆኑ ነገሮችን ማከናወን ኣለበት

   - ***ፈጠራ ያለባቸው:*** አዳዲስ አሰራር ወይ ቴክኖሎጂን መጠቀም ይህም እንደ አዲስ አፕን መፍጠር ወይን የጥገና ወርክሾፕን ወደ ሲያትል ማምጣት

     ***እና/ወይም***

   - ***ከሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ አንድ ወይን ከዚያ በላይ የሆኑት ማካተት:*** ነጭ ያልሆኑ፣ ስደተኞች፣ ጥገኞች፣ ዝቅተኛ ገቢያላቸውን፣ አካል ጉዳት ያላቸውን፣ አረጋውያንን፣ ወጣት አዋቂዎችን፣ ወጣቶች ልጆችን፣ እና/ወይም ትናንሽ ንግዶችን

     ***እና/ወይም***

   - ***እጠረት ውስጥ ያሉ ማህበረቦች መርዳት:*** ነፃ ወይም ዝቅተኛ-ወጪ ያላቸውን ግብዓቶች በማቅረብ የሰውን አቅም ያማከለ ማድረግ፣ ወይም ቤት ለሌላቸው ወይም ዝቅተኛ-ገቢ ላላቸው ማህበረሰቦች የስራ ስልጠና መስጠት

## ፈንድ እና ወጪ መጋራት መስፈርት

***ፈንድ፡***

- ለ 2019-20 ግራንት ኡደት አጠቃላይ $100,000 የሚሆን ገንዘብ አለ፡፡
- የግራንት ጥያቄ ከ $5,000 እስከ $20,000 ያክል ሊሆን ይችላል፡፡ SPU ከዚህ የሚያንስ ወይም የሚበልጥ መጠንን ግራንት ለማድረግ መብት አለው፡፡
- በገምጋሚው ኮሚቴ እና SPU አማካኝነት የሚፈቀደው ስጦታ ከተጠየቀው መጠን ሊያንስ ይችላል፡፡
- የግራንት ፈንድ የሚሰጠው እንደ ተከታታይ ክፍያ ነው፡፡ የተጠናቀቀው ፕሮጀክት አጠቃላይ ወጪ ከበጀቱ የሚያንስ ከሆነ፣ የሚሰጠው ገንዘብ እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡
- የግራንት ፈንድ ፕሮጀክቱ በተጀመረ በ 12 ወራት ውስጥ ሊያለቅ ያስፈልጋል፡፡ ግራንቱ የረጅም ጊዜ ግራንትን ለፕሮጀክቶች አይሰጥም፡፡ አመልካቾች ለአዳዲስ ወይም ማስፋፊያ ፕሮጀክት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

**የወጪ መጋራት መስፈርት፡**

- ወጪ መጋራቱ የተጠየቀውን ፈንድ ቢያንስ ግማሽ ሊሆን ያስፈልጋል (በከተማው ለሚሰጠው ገንዘብ እያንዳንዱ ዶላር 50 ሳንቲም ያለው ዋጋ)፡፡
- ብድር ለማግኘት አመልካቾች ዶክመንቱን ሊሰጡ ያስፈልጋል፡፡
- የወጪ መጋራት መዋጮ በአይነት ወይም ገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡
- የሲያትል ከተማ ግብአቶች ማለትም እንደ ከተማው ሰራተኞች ሰአት፣ የከተማውን መገልገያዎች መጠቀም እና/ወይም ፈንድ እንደ ወጪ መጋራት አይቆጠርም፡፡

**የኢንሹራንስ መስፈርቶች፡**

በጠቅላላው፣ ፕሮጀክቶቹ እነዚህ የሚከተሉት ኢንሹራንሶች ያስፈልጓቸዋል፡

- $1,000,000 በንግድ አጠቃላይ ኃላፊነት (CGL) ኢንሹራንስ
- $1,000,000 በንግድ ተሽከርካሪ ኃላፊነት ኢንሹራንስ ኢንሹራንሱ ለንግድ ተሽከርካሪው ብቻ ነው መዋል ያለበት፣ የግል ተሽከርካሪ ኢንሹራንስ አይደለም፡፡ ፕሮጀክቱ ተሽከርካሪ የማያካትት ከሆነ፣ ወይም ፕሮጀክቱ ፈቃድ ያላቸውን እና የንግድ ኢንሹራንስ ያላቸውን የትራንስፖርት መንገድ ወይም የማድረስ መንገድ የሚጠቀሙ ከሆነ ይሄ መስፈርት ሊነሳ ይችላል፡፡
- የሰራተኞች አበል ኢንሹራንስ

እንደየፕሮጀክቶቹ እያንዳንዱ የኢንሹራንስ መስፈርቶች ይለያያል፡፡ እንዲፈቀዱ በተመረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የኢንሹራስ መስፈርቶችን ለማወቅ SPU ይሰራል፡፡ ከመደበኛ ሽፋንዎ በተጨማሪ ለፕሮጀክት የተመደቡ የኢንሹራንስ ወጪዎችዎ በሽልማት ጥያቄዎ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፣ በሽልማቱ ከፍተኛ ድጋፍ ሊደረግላቸው የሚችለው $500 ነው፡፡

**የወጪ ምድቦች፡**

ሊከፈል የሚችል ወጪ እና ወጪ መጋራት ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ሊገናኝ ያስፈልጋል፡፡

- የወጪ መጋራቶች በማመልከቻው ቀን ላይ ሊጀመሩ ይችላሉ፡፡
- ተመልሰው የሚከፈሉ ወጪዎች ከከተማው ጋር ኮንትራት በሚፈረምበት ወቅት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

| | ተመልሶ የሚከፈል ክፍያ | ወጪ መጋራት |
|---|---|---|
| ለፕሮጀክቱ የተመደበ የሰራተኞች ሰአት (ተጨማሪ ሰአትን ሊጨምር ይችላል) | ✓ | ✓ |
| የፕሮጀክት አቅርቦት፣ እቃዎች እና መሳሪያዎች | ✓ | ✓ |
| ፕሮጀክት ጋር ግንኙነት ያላቸው አገልግሎቶች ማለትም እንደ ማስተርጎም፣ ህትመት እና ዲዛይን | ✓ | ✓ |
| ለፕሮጀክት ስራዎት የቦታ ኪራይ | ✓ | ✓ |
| ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ለማህበረሰቡ የዋለ ምግብ እና መጠጥ፣ አልኮል ያላቸውን መጠጦች ሳይጨምር<br>(ለፕሮጀክቱ በየሰው ያለው መጠን አግባብነት ያለው መሆን አለበት፣ ቢበዛ በሰው $10) | ✓ | ✓ |
| ለፕሮጀክት ተሳትፎ ማበረታቻ<br>(ለፕሮጀክቱ በየሰው ያለው መጠን አግባብነት ያለው መሆን አለበት) | ✓ | ✓ |
| ፕሮጀክት ጋር ግንኙነት ያለው መኪና ማቆሚያ እና በሲያትል ውስጥ ያለ ርቀት (በፌደራል ተመን መሰረት የሚከፈል)<br>(በፌደራል ማይሌጅ ተመን የሚከፈል) | ✓ | ✓ |
| የገንዘብ ያዥ ክፍያዎች<br>የፊስካል ወኪል ክፍ (ከአጠቃላይ የፕሮጀክቱ መጠን 10% በላይ ሊሆን አይችልም) | ✓ | ✓ |
| ከመደበኛ ሽፋንዎ በተጨማሪ ለፕሮጀክት የተመደቡ የኢንሹራንስ ወጪዎችዎ<br>(ለፕሮጀክቱ ውጤቶች የኢንሹራንስ መጠኑ አግባብነት ያለው መሆን አለበት፣ በሽልማቱ ከፍተኛ ድጋፍ ሊደረግላቸው የሚችለው $500 ነው) | ✓ | ✓ |

| | ተመልሶ የሚከፈል ክፍያ | ወጪ መጋራት |
|---|---|---|
| የበጎ ፈቃደኞች ለፐሮጀክት የሚመደብ ሰአት (በ$24/ሰአት የሚሰላ) | | ✓ |
| ከፐሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያለው ከከተማ ውጪ የሚደረግ የጉዞ ወጪ | | ✓ |
| ለፐሮጀክቱ የሚውሉ ሌሎች የተፈቀዱ እርዳታዎች ወይም የገንዘብ መዋጮ<br>(ከሲያትል ከተማ ሌሎች እርዳታዎችን አይጨምርም) | | ✓ |

## የማመልከት ሂደት

**መርሀ ግብር፡**

| | |
|---|---|
| **ማመልከቻ ማስገቢያ ማብቂያ ቀን** | መጋቢት 22፣ 2019 |
| **የውሳኔ ማሳወቂያ** | ግንቦት 2019 |
| **ከከተማው ጋር ኮንትራት መፈራረም** | በ ጁላይ 2019 ላይ |
| **ስራው የሚጀመረው** | ጁላይ-ኦክቶበር 2019 |
| **ስራው የሚጠናቀቀው** | ፐሮጀክት በተጀመረ በ 12 ወራት ጊዜ ውስጥ ማለት ነው |

**የማመልከት ሂደት**

**ደረጃ 1: መመርያዎቹን ያንብቡ**

**ደረጃ 2:** እኛን ያግኙ

- ፐሮጀክትዎ ብቁ ስለመሆኑ ያረጋግጡ
- ስለ መመሪያው እና ማመልከቻው ጥያቄዎችን ይጠይቁ

**ደረጃ 3፡ ከግራንት መረጃ መስጫ ክፍለ ጊዜዎች እንደኛው ላይ ይሳተፉ (የሚፈልጉ እንደሆነ)**

| **ሰሜን ሲያትል** | **መካከለኛ ሲያትል** | **ደቡብ ሲያትል** | **ምዕራብ ሲያትል** |
|---|---|---|---|
| ጃንዋሪ 15፣ 2019 | ጃንዋሪ 26፣ 2019 | ፌብሩዋሪ 4፣ 2019 | ፌብሩዋሪ 9፣ 2019 |
| 5:30-7:00 PM | 12:00-1:30 PM | 5:30-7:00 PM | 12:00-1:30 PM |
| Green Lake ቤተ-መፃህፍት | Montlake ቤተ-መፃህፍት | Columbia ቤተ-መፃህፍት | Delridge ቤተ-መፃህፍት |
| 7364 E Green Lake Dr N | 2401 24th Ave E | 4721 Rainier Ave S | 5423 Delridge Way SW |

እባክዎትን ቋንቋ ማስተርጎም አገልግሎትን ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ይጠይቁ **ይህም ቢያንስ አንድ ሳምንት** መረጃው ከሚሰጥበት ጊዜ በፊት ማለት ነው፡፡

**ደረጃ 4፡ እስከ መጋቢት 22 2019 ድረስ የግራንት ማመልከቻዎትን በጽሁፍ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል/ ቪዲዮ ፎርማት ያስገቡ፡፡**

- የወረቀት ማመልከቻ ፎርም (ከ 7 ገጽበላይ ሊሆን አይችልም 7)
- የቪዲዮ ማመልከቻ መመሪያ (ከ 20 ደቂቃዎች መብለጥ የለበትም)
- የማመልከቻ በጀት ፎርም (ለወረቀት ሆነ ለቪዲዮ ማመልከቻ)

ማመልከቻዎች በሚፈልጉት ቋንቋ ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡ SPU የትርጉም/ማስተርጎም አገልግሎት ይሰጣል፡፡

# የማመልቻዎች ክለሳ

**የክለሳው ቡድን፡**

የግራትንት ክለሳው ቡድን ከማህበረሰብ አባላት እና የሲያትል ከተማ ሰራተኞች የተወጣጣ ሲሆን  የተለያዩ ልምድ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው፡፡

**የክለሳው መስፈርት**

ፕሮጀክቶች በመጀመሪያ የፕሮጀክቱን መስፈርት እንደሚያሟሉ ይረጋገጣል፡፡ ከዚያም የግራንት ክለሳው ቡድን ብቁ ናቸው የሚባሉ ፕሮጀክቶችን በስድስት የመመርጫ መስፈርቶችን መሰረት ደረጃ/ዋጋ ይሰጣል፡፡ SPU የአካባቢ ብዝሀነትን፣ ተጽእኖ የተደረገባቸውን ማህበረሰቦችን እና የፕሮጀክት አይነቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

1. **(30%) ብክነትን መከላከል:** አንድ ፕሮጀክት ብክነትን ለመከላከል ያለው አቅም፡፡
    - ፕሮጀክቱ ስኬትን ለመመዘን ይችላል?
    - በፓውንድ ሊቀነስ የሚችለው መጠን ምን ያክል ሊሆን ይችላል እና በብክነት ውስጥ የሚገቡት ምን ያክል እቃዎች ናቸው?
    - በማህበረሰቡ ተደራሽንት እና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ያለው እድል ምን ያክል ነው?
    - ግራንቱ ካለቀ በኋላ የብክነት መከላከል ውጤቱ እስከ ምን ያክል ጊዜ የሚቆይ ይሆናል?

2. **(15%) ፈጠራ:** ፕሮጀክቱ አዲስ አቀራረብ ወይም ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ያውላል፡፡
    - ፕሮጀክቱ አዲሱን አቀራረብ ወይም ቴክኖሎጂ የሚመዝው ወይም የሚያስፋፋው እንዴት ነው?
    - ፕሮጀክቱ ሌሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ሰዎች ተስፋፍቶ መገልገል ይችላል?
    - የፕሮጀክት ዘዴ እና  ውጤቶች ከማህበረሰቡ ጋር መደጋገፍ ወይም የልምድ ልውውጥ አንዴት ይከናወናል?

3. **(15%) የማህበረሰብ ተሳትፎ:** ማህበረሰቦችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መከላከል/እንደገና ለመጠቀም ላይ ማሳተፍ የመቻል አቅም፡፡
    - ፕሮጀክቱ አሳታፊ የሆኑ ስልቶችን ይጠቀማል?
    - በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ማህበረሰብ አባላት በእቅድ እና ትግበራው ላይ እንዴት አድርገው ነው መሳተፍ የሚችሉት?
    - ፕሮጀክቱ ከማህበረሰቡ ጋር በጣምራ የሚሰራው አንዴት ነው?
    - ብዝሀነትን ማለትም፥  ስደተኞችን፣ ጥገኞች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን፣ ወጣት አዋቂዎችን፣ ወጣት ልጆችን እና/ወይም ትናንሽ ንግዶች አንዴት አደርጎ ነው ፕሮጀክቱ የሚያሳትፈው?

4. **(15%) የማህበረሰብ ጥቅም:** ፕሮጀክቱ ለማበረሰቡ ጥቅም የመስጠት አቅሙ፡፡
    - ፕሮጀክቱ ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚሰጠው (ማለትም የአካባቢውን ጤና የሚየሻሽላ፣ ስራ መፍጠር ወይም ክህሎት ማሳደግ ወይ ዝቀተኛ ወጪ ወይም ነጻ ግብአቶችን መስጠት) የሚችለው እንዴት ነው?
    - ፕሮጀክቱ ይበልጥ ፍላጎት ላላቸው ማለትም ቤት ለሌላቸው ወይም ዝቅተና ገቢ ላላቸው ማህበረሰቦች ጥቅም የሚሰጠው እንዴት ነው?

5. **(15%) የፕሮጀክት አቅም:** በአቅሙ መሰረት አንድ ፕሮጀክት ስኬታማ ለመሆን ያለው እድል፡፡
    - ፕሮጀክቱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ በቂ ሰራተኞች፣ አጋሮች፣ በጎ ፈቃደኞች እና የገንዘብ አቅርቦት አለው?
    - ሽርክናዎች አስቀድሞ ዋስትና አግኝተዋል?
    - ፕሮጀክቱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ አውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ እና ከሌሎች ጋር ገንኙነት አለው?

6. **(10%) በጀት:** በተጠየቀው በጀት መሰረት ፕሮጀክቱ ስኬታማ የመሆን እድሉ ምን ያክል ነው፡፡
    - በጀቱ ከፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ጋር አንድ አይነት ነው?
    - የበጀት ግምቶቹ ትክክል ናቸው?
    - ለግራንት የሚሰጡ ሁሉም ወጪዎች ትክክል ናቸው?
    - የተጠየቀው ገንዘብ ይደረስበታል ለተባለው ውጤት ይመጥናል?

# ኮንትራት እና ክፍያ

**ኮንትራት**

- ሽልማቱን የሚቀበሉ እርዳታውን ለመቀበል የዋሽንግተን ስተት እና የሲያትል ከተማ ንግድ ፍቃድ ያስፈልጋቸዋል፣ ወይም በሚያስፈልገው ፈቃድ በገንዘብ ያዥ ሰራትኛው በኩል መስራት ያስፈልጋል፡፡
- ግራንት ያገኙ ይህንን ገንዘብ ለማግኘት ከ SPU ጋር ኮንትራት መፈራረም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኮንትራቱ ተጨማሪ ደንቦችን እና ሁኔታዎችን የሚያካትት ይሆናል፡፡
- ግራንት ተቀባዮች ግራንታቸውን ራሳቸው ሊያስተዳድሩ ወይም ፊስካል ወኪልን ጥቅም ላይ ሊያውሉ ይችላሉ፡፡ የፊስካል ወኪል ክፍያ ወጪ ከግራንቱ ሊደረግ ይችላል ወይም እንደ ወጪ መጋራት ሊያዝ ይችላል፡፡ ፊስካል ወኪልን የማይጠቀሙ የግራንት ተቀባዮች የራሳቸውን የግብር ከፋይ መለያ ሊያመጡ ያስፈልጋል እንዲሁም ለውስጥ ገቢዎች አገልግሎቶች ህግ መገዛት አለባቸው፡፡
- ግራንቱ ሽፋን የሚያደርግላቸው ወጪዎች ኮንትራት ፍርርም ከተካሄደ በኋላ ያሉትን ብቻ ነው፡፡

***ገንዘብ ያዥ ሰራተኛ፡***

- አመልካቾች በገንዘብ ያዥ ሰራተኛው በኩል ለፕሮጀክቱ የሚደረገውን እርዳታ ለመቀበል እና ለማስተዳደር ሃላፊነት እንዲወስድ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡
- አመልካቾች የራሳቸውን ገንዘብ ያዥ ሰራተኛ የመለየት እና ገንዘብ ያዥ ሰራተኛው በጊዜው የዋሽንግተን ከተማ እና የሲያትል ከተማ የንግድ ፍቃድ እንዳለው የማረጋገጥ ሃላፊነት አላቸው፡፡
- ገንዘብ ያዥ ሰራተኛው ከተፈቀደው ሽልማት እስከ 10% ሊወስድ ይችላል፡፡  ይህንን ክፍያ ከፕሮጀክቱ በጀት ውስጥ መጨመር ይችላሉ፡፡

**ክፍያ፡**

ግራንት ያገኙ ከፕሮጀክት ጋር ለተያያዘ ወጪ በየወሩ ወይም በሶስት ወር አንድ ጊዜ ክፍያ ደረሰኝ ይልካሉ፡፡ SPU የካሳውን ቼክ ደረሰኙን ከተቀበለ ከአራት ሳምንት በውሃላ በፖስታ ይልካል፡፡ ደረሰኙ ካልተሟላ ወይም የሚያስፈልግ መረጃ እና መግለጫ ከጎደለ ክፍያው ይዘገያል፡፡

***ሪፖርት፡***

- የግራንት ተቀባዮች በእያንዳንዱ ደረሰኝ ላይ የሂደት ሪፖርትን ማስገባት ያስፈልጋቸዋል፡፡
- የመጨረሻውን የግራንት ክፍያ ከማገኘታቸው በፊት፣ ግራንት ያሸነፉ በሙሉ የፕሮጀክቱን ውጤት እና የተማሩትን ትምህርት ሪፖርት ሊያካትቱ ያስፈልጋል፡፡ ሪፖርቱ በ SPU ድረገጽ ላይ ፖስት ሊደረግ ይችላል

# አኛን ያግኙ

አድራሻ  wastefreegrants@seattle.gov ወይም (206) 684-7868 በእንግሊዘኛ ወይም ከዚህ በታች  ባልተዘረዘሩ ቋንቋዎች እርዳታ ለማግኘት ፡፡

በሚከተሉት ቋንቋዎች እርዳታ ለማግኘት አጋራችንን ECOSS ን በ info@ecoss.org ላይ ወይም (206) 767-0432 የውስጥ መስመር 1009 ላይ ያግኙ፡፡ መልእክቶን ያስቀምጡ እና አንደ ሰው መልሶ ይደውልልዎታል፡፡

- አማርኛ
- ካንቶንኛ
- ከመርኛ
- ኮርያኛ
- ቻይንኛ
- ሶማልኛ
- ስፔንኛ
- ትግርኛ
- ቬትናምኛ